# የፊንፊኔ ፖለቲካ ፣ የቅማንንት አገው አንድነት፣ የእነ ገዱ ቡድን ተቃውሞ፣ዐማራ መሳይ ዐማራን ከፋፋይና የህወሃት የቀን ቅዠት!

በአዲስ ተስፋ

ዶክተር አብይ ሰሞኑን ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ባደረጉት ውይይት የሚገባቸው ከሆነ ለተቃዋሚዎች እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ የሆነ መወዳደሪያና ማሸነፊያ መንገድ ጠቁመዋቸዋል።ለመሆኑ ይህ ጥቆማ ምንድነው?ወደ አራትና ሶስት ዝቅ ብትሉ ይሻላል የተባለላቸው ፓርቲዎችስ ይጠቀሙበት ይሆን ወደ ዚህ ሃሳብ ከመመለሴ በፊት ስለፊንፊኔ ፖለቲካ ትንሽ ማለት ፈለግሁ። አነጋውያን የተሰተፉበት የአዲስ አበባ ብጥብጥና ንጹሃን ወጣቶችን ወደ እስር ቤት ማጓዝ ተጀምሮበት የነበርው ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ህዝብ ታጋሽነት በተለይም በሸገሮች አርቆ አሳቢነት የተጨናገፈ ቢመስልም የልብ ትርታን ለመለካት መጠቀሚያ የሆነው የፊንፊኔ ፖለቲካ አሁንም ቀጥሏል። የኤል ቲቪዋ በተልሄም አዲስ አበባ የማን ናት ጥያቄዋን ከፖለቲከኛ እስከ ዘፋኝ ከምሑራን እስከ ተማሪ ከነዋሪዎቿ እስከ ባእዳን ድረስ መጠየቋንና አነጋጋሪ መልሶች መሰጠቱ ቀጥሏል። በጥያቄው አስፈላጊነት ብዙ ማለት ቢቻልም በአጭሩ መጠየቅ ያልነበረበት እንደነበር ግን አብዛኛው ሰው ይስማማል። አዲስ አበባ የነዋሪዎች ነች። በምንም መስፈርት ይህንን ትርጉም የሚያዛባ መልስ ትክክል ሊሆን አይችልም። አመስተርዳም የማን ነች? የነዋሪዎች ነች በሚለው አባባል የውጭዜጋን አምርሮ የሚጠላው ፖለቲከኛ ጌርት ቪልደርስ ልዩነት የለውም። በ አምስተርዳም ከተማ የሚኖረው አሜሪካዊም ሆነ ራሺያዊ ህጋዊ ፈቃድ እስካለው ድረስ ባለቤትና ነዋሪ ነው። አንድም ሰው አምስተርዳም የሰሜን ሆላንድ ወይም የደቡብ ሆላንድ ነች አይልም። ምሳሌየን ያለምክንያት አላመጣሁትም። የሀገራችንን ፖለቲካ አራማጆች ስለፌደራሊዝም ሲያዎሩ ብዙ ጊዜ ኔዘርላንድን እንደምሳሌ ስለሚያነሱ ነው። የኔዘርላንድ ዋና ከተማ አምስተርዳም በሰሜን ሆላንድ ፕሮቪንስ ተገኛለች። ነገር ግን አንድም ሰው አንድም የሰሜን ሆላንድ ነዋሪ አምስተርዳም የእኔ ነች ሲል አይሰማም። አምስተርዳም የነዋሪዎቿና የነዋሪዎቿ ብቻ ነች። ለነገሩ አንዱአስገራሚ የኢህአዲጋውያን ስህተት የያዙት የዘር ፈደራል ስርዓት ከኔዘርላንድ ፈደራሊዝም ጋር አንድ ነው ማለታቸው ነው። ኔዘርላድ ያላትን የፌደራላዊ ስርዓት ማንም ኢትዮጵያዊ የሚመኘው ነው። ምክንያቱም የኔዘርላንድስ ፈደራላዊ አዎቃቀር በ12 አውራጃዎች የተከፈና ዘርን ያልተከተለ ነው። ዘር ወይም ቋንቋ የሚባል መከፋፈል ፈጽሞ የለም። ከአስራ ሁለቱ አውራጃዎች አንደኛው አውራጃ የራሱ ቋንቋ ያለው ቢሆንም የብሄራዊ ቋንቋቸው ግን አንድና አንድ እርሱም ደች ነው።ሁልጊዜም የኢትዮጵያን ፌደራላዊ ስርዓት ከኔዘርላድስ ፈደራላዊ ስርዓት ጋር ሲነጻጸር ይገርመኛል። በምንምና በምንም አይገናኝም ።

ቋንቋና ዘርን በፍጹም ያማከለ አይደለም። ከካርታው መመልከት እንደሚቻለው መልካምእድርን መሰረት ያደረገ የአስተዳደር ቅርጽ ነው ያለው። ፌደራላዊ ስርዓት የሚባለውም አውራጃዎች ያልምንም ጣልቃግብነት ግዛታቸውን ማስተዳደርና ማልማት መቻላቸው ብቻ ነው። የትኛውም ዜጋ በፈለገው የመኖር ብቻ ሳይሆን የትም የምስራት መብት አለው። የወንጀል ሪከርድ የሌለበት የትኛውም ዜጋ በፈለገው ጊዜ በፈለገው አመት ያለበትን ፕሮቬንሲ መቀየር የፈለገበት ቦታ የመኖር መብት አለው። ታዲያ ይህ ፌደራላዊ ስርዓት ከኢትዮጵያ ኦሮሞ አማራ አይነት ክልል ጋር እንዴት ነው የሚመሳሰለው ? ክልላችንን ለቀህ ውጣ ከሚባል የአውሬነት ባህርይ ከሚያላብስ አከላለል ጋር እንዴ ት ነው አንድ የሚሆነው?በመጀመሪያ ደረጃ አገራችን የሁላችን ነች። የመቀሌውም ሆነ የነቀምቱ በፈለገው ጊዜ ተነስቶ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ የመኖር መብቱ መጠበቅ ይገባዋል።ሃረርም ሆነ ጎጃም የተወለደ ወደ አዲስ አበባ የመግባትና የመኖር መብታቸው መሸራረፍ የለበትም። ከፋም ሆነ ጎንደር ወሎም ሆነ አሉአባቦር ጋሞ ጎፋም ሆነ ሲዳሞ አልያም ባሌ አንዱ ወደሌልው የመዬድና የመኖር ሃብት የማፍራትና የመንቀሳቀስ መብት በ አማራ ችሮታ አልያም ኦሮሞ ስለፈቀደ ወይ ደግሞ አፋሩ ደስ ስላለው ሳይሆን አገራችን በመሆኑ ብቻ ያለገደብ በየትናውም ቦታ የመኖር የዜግነት መብት በማንም ሊነፈግ ወይም ሊሰጥ አይገባውም። በዚህ አግባም ኦሮሞውም ሆነ አማራው ወይም ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ አዲስ አበባ የእኔ

ነች ቢል ምንም ስ ህተት የለውም።አሁን ቤተልሄም በምትጠይቀው አውድ ወይም ሃጫሉ ሁንዴሳ በመለሰበት አኳሆን ወይም  አምስቱ የኦሮሞ ድርጀቶች ባዎጡት መግለጫ አውድ ግን ፍጽሞ ሊሆን አይችልም።




ወያኔያውያን የኔዘርላንድን  ፌደራላዊ አከላለል ተከትለናል የሚሉትና ፈጸሞ የተለየ የሆነው የኔዘርላድ አውራጃዊ አከላለል።

በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ገበሬዎች ከተማዋ ስትፋፋ  በሚገጥማቸው መፈናቀል አስፈላጊውን ካሳ የሚያገኙበትንና እንዲያውም ተጠቃሚ እንጂ ተጎጅ የማይሆኑበትን መንገድ መቀየስ የከተማዋ አስተዳደር

ወይም የሃገሪቱ ሃላፊነትመሆን ያለበት መሆኑን አምናለሁ። የኦሮምያ ክልል የሚያገኘው ጥቅም ወይም ሌላ ዝባ ዝንኬ ግን ሆን ተብሎ የተዘጋጀ የልዩነት መፍጠሪያ እንደነበር መገንዘብ አስፈላጊ ነው።ኦቦ በቀለ ገርባ ወይም ሃጫሉ የሚሉበት አውድ ግን ሰዋዊ አይደለም። አዲስ አበባ የማነች የበተልሄም ጥያቄ አስተዛዛነቱ ብቻ ሳይሆን ምንም የማያውቁ ደግና ሩህሩህ የሆኑ የገጠር ማህበረሰቦቻችን ሳይቀር በእኔ ነው የህልም ቅዠት እንዲንሰፈፉ በማድረግ የምንጠቀመው ጥቅም የለምና እባካች ሁ ወደ አቅላችሁ ተመለሱ።የፌንፌኔ ፖለቲካ ስነ ልቦናዊ ጦርነት ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይም አዐማራና ኦሮሞ እርስ በእርሳቸው እንዳይተማመኑ ለማድረግ የተሰራ ከንቱ ተንኮል ነው። በመሰረቱ ተጠቃሚው ማን እንደሆነ በከተማይቱ ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን ማን እንዳቆመ የሚታወቅ ሆኖ እያለ ይህም ተራ ሻጥር ሁለቱን ታላላቅ ህዝቦች ለማጋጨት መሆኑን ልብ ይሏል።

ባለፉት ጥቆማዎቼ በኦነግ ላይ ማነጣጠሬም ህዝቡ ከምንም በላይ መረዳት ያለበት የስርዓቱን መሰሪነት ነው ለማለት የተጠቀምኩበት ነው። አሁን ህወሃት ሞቷል። በፖለቲካው ከተሸነፈ አማታት ቢያስቆጥርም አሁን ግን በሁሉ ረገድ ተሸንፏል። በስነ ልቦና ተሸንፏል፣ ከስልጣኑ ተባሯል፣ ዋና ዋና የሆኑ የሰራ ፖለቲካው ማራመጃዎች በህዝቡ ንቃት ተደርሶባቸዋል።በየክልሎች ያስቀመጧቸው የጡት አባቶች ተነቅቶባቸው ሸባ ሆነዋል። አሁን ያላቸው ከህዝቡ የሰረቁት ገንዘብና ህሊና የሌላቸው ተላላኪዎች ብቻ ናቸው። ዛሬ ቤንሻንጉልና ጋንቤላን ይዘው ሊገነጠሉ ነው የሚለው ተረት ተረት ዘመን አልፎበታል። ጥቂት ባንዳዎችን በመያዝ በቅማንት ማንነት ጥያቄ ስም ሊያዋቅሩት የነበረና ከጋምቤላና ቤንሻንጉል ጋር የሚያዋስን ድንበር ለማግኘት የተሞከረውና ላለፉት ብዙ አመታት የተሰራበት ፍኖተ ካርታ የተቃጠለ ፊልም ሆኗል። መተከልም ለዘመናት ካደራጀውና ከኖረበት ቀየው ጎጃም ጋር የሚቀላቀልበት ጊዜ እየተናነቃቸውም ቢሆን ደርሷል። ድሮም መሬት እንጂ ሰው የማይፈልገው ዘረኛ ቡድን እስካሁን የእግር እሳት የሆነበት ትግሪኛ የሚናገረው ኮሎኔል ዘውዱ አማራነቱን አንግቦና ለአማራ ወኪል ሆኖ መቅረቡ ነበር። ዛሬም የህወሃት ባለስልጣናት ስለኮረኔሉ በነጻ መንቀሳቀስ መስማትና ማየት ያቃጥላቸዋል።አውቀውም መቀበል ያቃታቸው ግን ዐማራው በቃች ሁኝ እንዳላቸው ነው። ከእንግዲህ አይደለም በጎንደር፣ በባህርዳር፣ በደሴ፣ በደብረታቦር፣ በደብረብርሃን፣ በደብረማርቆስ፣ በኮምቦልቻ፣ በፍኖተሰላን፣ በቡሬ፣ በዳባት፣ በጋይንትና ሌሎች የአማራ ባሏቸው ከተሞች ቀርቶ ዐማራ በሚገኝበት በየትኛውም ቦታ ከ ዐማራ ጋር መታገልና ማሸነፍ አይችሉም። የኢኮኖሚ ኢምፓየርም መገንባት አይችሉም።እንዴት ቢሉ በራእያ ወጣቶች ላይ የሞከሩትንና ውጤቱን አይተዋልና። ለምን ቢሉ በኮሎኔል ደመቀ የግድያ ሙከራ የደረሰባቸውን ውርደት ያውቃሉና። ለምን ቢሉ የናቁት የወልቃይት የማንነት ጥያቄ እንዴት ከመሰረታቸው ፈንቅሎ እንዳስወረዳቸው ያውቃሉና። ዐማራ መጀመሪያ እስኪነሳ እንጂ ከተነሳ ድንጋይና በትር ይዞ ዘመናዊ ጦር የታጠቀን ገጥሞ ማሸነፍ የሚችል እንደሆነ ያውቃሉና። በምን ምክን ያት ቢባል ደርግ ተደምስ ሶ ስተት ብለው የምኒልክ ቤተመንግስት እንዲገቡና ይህንን ያህል ዘመን እየዘረፉ እንዲኖሩ የሆኑት መንገድ ከፍቶ ያለምንም ተቃውሞ ስላለቀቃቸው እንደሆነ ያውቃሉና። የዐማራ ህዝብ ይህንን መሰሪነታቸውንና ራሱን ለማጥፋት ፕሮግራም ቀርጸው እንደሚሰሩ ቢያውቅ ኖሮ እንኳንስ አዲስ አበባ ከዎሎ ውይም ከጎንደር አንዲት ጋሻ መሬት ሊያሳልፋቸው እንደማይችል ጠንቅቀው ያውቃሉና።ህወሃትና ጋሻዣግሬዎቹ ከዐማራ ጋር ጦርነት ሊገጥሙ ነው በዝግጅት ላይ ናቸው እያሉ አንዳንድ የዋሃን ያስተጋቡላቸዋል። የስነልቦና ጦርነት መሆኑ ነው። ህውሃይ ይህንን ፍጽማ አታደርግም። በህልምም አታስበውም። ለ ዐማራ ህዝብ አዝና ወይም ዘመናዊነት ተሰምቷት ሳይሆን የሚደርስባትን ኪሳራ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ አስከፊ ውጤቱን ታውቃለቻ። ዐማራ እንዳመረረባት ከማንም በላይ ተረድታለች። አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸትታለች ነው የሚሆነው። ምናልባትም ቬሮኒካ መላኩ የተባሉ ጸሃፊ እንዳሉት በአለማችን የመጨረሻ አጨሩ ጦርነት ሊሆን የሚችለው ህወሃት አማራን እገጠማለሁ ብላ ከተነሳች የሚደረገው ጦርነት ይሆናል።ባጎረስኩ ተነከስኩ የሆነበት ዐማራ ለህወሃት ቅንጣት ያክል ርህራሄ የለውም። ይህንን በሚገባ የተረዳችው ህወሃት ትኩረት ለማስቀየር በተባባሪዋ አክራሪና ጽንፈኛ ቡድን በኩል የፊንፊኔን ፖለቲካ ታራግብብብን ከጀመረች እነሆ ወራት ተቆጠረ። የዚህ ፖለቲካ የህዝብ ግንኙነት ሆና እያገለገለች ያለችዋን የኤል ቲቪ ጋዜጠኛም ያለውቀት ከሆነ እባክሽ ይቅርብሽ ብሎ የሚመክራት ሰው ያስፈልጋል።አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የዐማራውን መደራጀት ፣ መገስገስና ኢትዮጵያን ለመታደግ የሚያደርገውን ጥረት ለማቆም የሚጥሩ ለምን በአማራ ስም ትደራጃላችሁ ብለው ጉንጭ አልፋ

ልፈፋ የቀጠሉ ሰወችም ሃይ ሊባሉ ይገባል። በቅርቡ አንድ ሰው ደጉ አንዳርጋቸውን ለምን ስማችሁን የአማራ ብሄራዊ ፓርቲ አላቸሁ ብሎ በማለት ሲሞግተውና ኢትዮጵያን ለማፍረስ የተደረገው ጥረት አሁንም አልቆመም በማለት ጸረ ዐማራ ቡድኖችን ሲያስጨበጭብ አይቻለሁ። አሁን ባለው ሁኔታ ዐማራዊ ስምን ማጥፋት ሳይሆን ዐማራዊ ፓርቲዎችን ማጠናከር የዎቅቱ አንገብጋቢ መፍት ሄ መሆኑ ማንም ሊያውቀው የሚገባ ታላቅ እውነት ነው።

ሰው በላው የህወሃት ቡድን ከየትኛው የጎሳ ድርጅት ይልቅ ዐማራ መደራጀቱ የማያባራ ፍርሃት ውስጥ ከከተተው ውሎ አድሯል። ለዚህ ቡድን የሶማሊያና ኦሮሞ ግጭት አያሳስበውም። በርካታ ኦሮሞዎች በታጣቂ ቡድኖች መገደላቸውና ከቤት ንብረታቸው መፈናቀላቸው ምኑም አይደለም። የጌድዮና የጉጅ ኦሮሞዎች እርስ በእርስ መፋጀትም ደስታው ቢሆን እንጂ አያሳዝነውም። ሁሉንም ግጭቶች ስፖንሰር የሚያደርገው ይሄው ዘረኛ ቡድን በመሆኑ በሌሎች ስፍራዎች ሁሉ ያለው ግጭት አያስፈራውም። ነገር ግን የዐማራው ንቃትና ዘረኝነትን በቃኝ ብሎ መነሳት እጅግ ብርክ አስይዞታል። በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ የመህበራዊ መገናኛ ብዙሃን ሰራተኞችን ያሰማራውም በዐማራ ላይ እንጂ በማንም ልይ አይደለም። ገዱና ደመቀን ለማስወገድ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም። እነኢህ ሰዎችና ደጋፍዎቻቸው አስቀድመው የዚህ ቡድን አገልጋይ የነበሩ ቢሆንም አሁን ከህዝባቸው ጋር መሆናቸው የእግር እሳት የሆነበት ወያኔ ዐማራውንና የእነ ደመቀን ቡድን ለመለያየት ቀድሞ ሲያስወራው ከነበረው በሬ ወለድ ታሪክ ሲነቃበት አሁን ደግሞ ለየት ባለና ለዐማራው አልቆሙም በሚል የአዛኝ ቅቤ አንጓች አቀራረብ መጥቷል። ለዚህም በማስተዋል በሰሜን አሜሪካ ከእነ ደጉ ጋር የተደረጉና የተነሱ ጥያቄና መልሶችን ማስተዋል ብቻ በቂ ነው። ለሃያ ሰባት አመት በወያኔ ሲረገጥ፣ የገደልና ሲሳደድ የኖረው የዐማራው ህዝብ አሁን ያገኘውን ቢያንስ የመደራጀትና ስለጠላቱ የመገንዘብ ድል ምንም እንዳልሆነ በማጣጣል እነ ኦቦ ለማን በማሞገስ የዐማራው መሪዎች ግን ምንም እንዳልፈየዱ በመልፈፍ ዐማራን ባይታወር ለማድረግ ሲሞከር መስማትና ማየት ያሳዝናል። ደጉ  የቅማንትን ጥያቄ በስሜታዊነት እንዲጨፈልቅና በወያኔ ወጥመድ እንዲዎድቅ የሚገፋፉ ቁጩቶች ውስጠወይራነታቸውን ላላየ ለዐማራው መቆርቆር ይመስላል። ወያኔ ዘርፎ በለገሳቸው የድሃው ህዝብ ገንዘብ ስፖንሰር የሚደረጉ በዐማራ ስነ  ልቦና ላይ እንዲጫዎቱ የተላኩ ቅጥረኞች ቅማንትና አገው አንድ ነው ባሉበት አንደበታቸው አማራና አገው ግን የተለያየ ነው ብለው በአደባባይ ሲናገሩ አያፍሩም። በመሰረቱ ዘረኛው ህወሃት እንደሚለው ሳይሆን በ አካባቢው የሚኖሩት ኦሮሞዎችም፣ ቅማንቶችም፣ አገዎችም፣ አማራዎችም፣ ትግሬዎችም ፣አፋሮችም ሆኑ ሌሎች አንድ ህዝብ ናቸው። ቅማንት ከአማራ የተለየ ስነ ልቦና አለኝ እንዲል አገው ከአማራ እለያለሁ የሚል ጥያቄ እንዲያቀርብ ለምንና መቼ እንደተደረገ ሁሉም ዐማራ ያውቃል። እናም ይህች የዐማራ ህዝብ እርስ በእርስ እንዲፋጅ የተቀመመች መርዝ በገዱ ስሜታዊነት አገውንና ቅማንንትን በማሰርና በመግደል ተግባር ላይ እንድትውል የሚፈልጉ ወገኖች ለምን የአንድ ቀበሌ ህዝብ መላውን የዐማራ ህዝብ ያውካል በማለት እነ ገዱ እንዲዎገዙ ሲሰራ ለቀባሪ አረዱት ሙከራቸው ያስተዛዝባል። ወያኔ የነጋበት ጅብ ሆኗል። አገውም ሆነ ቅማንንት የወያኔ መተቀሚያ የሚሆንበት እድል አክትሟል። ከእንግዲህ ሁሉም ሙከራ የተበላ እቁብ ነው።በቤንሻንጉል ክልል በሁለተኛ ደረጃ ቁጥር ያለው የዐማራ ህዝብ ልዩ ዞን ወይም የክልል ጥያቄ ሳያቀርብ ከአንድ ሺህ ስድስት መቶ ያልበለጠ ቋንቋ ተናጋሪ ያለው የቅማንንት ማህበረሰብ ከአማራ የተለየሁና የዐማራ ስነ ልቦና የሌለኝ ህዝብ ነኝ አለ የሚለው ተረት ተረት ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም ጉዞ ነው። ለማንኛውም ወያኔ በፖለቲካ ከተሸነፈ የቆየ ቢሆንም ወደመቃብር አዎራረዱ ግን በዐማራው አንድነት ሊፈጸም ዝግጅት ላይ ነው።

ወያኔዎች ለዐማራ ህዝብ ያላቸው ጥላቻ ከአገር ወዳድነቱ ከጀግንነቱና ለብነትንና ሃሰትን ከመጸየፉ የመነጬ እንጂ ከሌላ ከምንም መነሻ አይደለም። ከዐማራ ይልቅ ሱዳኖች ይሻሉናል ማለት ምን ያህል የዘቀጠ አስተሳሰብ እንዳላቸው የሚያስረዳ እንጂ ገዱም ከትግራይ ይልቅ ሱዳኖች ይሻሉናል እንዲል እንድንጠብቅ የሚያደርግ አይደለም።  ወያኔ የሞተ ቢሆንም ወደመቃብር እስኪዎርድ ድረስ  በቅማንንት ስም የሚደረግ መከፋፈል፣ በአገው ስም የሚሰራ ሻጥርና የፊንፍኔ ፖለቲካ ቀጣይነት ቢኖረውም የወሬ መዳረሻ ከመሆን ውጪ ሌላ ፋይዳ

የለውም። ለዚህ ጥብቅ ማስረጃ ካስፈለገ ከወራት በፊት የዐማራን ማህበረሰብ መረጋጋት ለማጠፋት የምታደርጉትን ሻጥር አቁሙ ፤ ይህ ህዝብ አገር የመሰረተ ፣ ሌሌሎች የሚኖር ፣ ታጋሽና ለዐለም ምሳሌ የሆነ የጀግንነት ሞዴል ነው ፣ አሁን ነቅተናል፣ ገብቶናልም በማለት መርዷቸውን ለወያኔዎች የነገረ የኮሶበር ትንታግ የሆነ አገው ወጣት ነበር። የዚህ አገው ወጣት ማንንም ያለመፍራትና እውነታውን በአደባባይ መናገር ያጀገናቸው የአዊ ዞን ህዝብ በለፈው ሃያ ሰባት አመት የተሰራውን ሻጥር በመበጣጠስ የወያኔ ቅጥረኞች ባጠገባቸው እንዳይደርሱ አስጠንቅቀዋል። አገውንና ቅማንንትን እንወክላለን ብለው በመቀሌ ቤተመንግስትና በውጭ አገር ያሉት ምንደኛ መሆናቸውን ተገንዝበው በረጋ መንፈስ ሁሉንም እየታዘቡ ናቸው። ይህንን ንቃት ያልወደደው ወያኔ አሁን ደግሞ አማራ በመምሰል በ አገውና ቅማንንት ላይ ደጉ እርምጃ እንዲዎስድ ካልዎሰደ ግን የወያኔ ተላላኪ እንደሆነ በመንገር እንዲሸማቀቅ ለማድረግ የሚደረገው ሙከራ እንተወው ብለን እንጂ የዝምብ ጠንጋራ እናውቃለን እንድንል አስገድዶናል። በመጨረሻም ወደተነሳሁበት መንደርደሪያ ልመለስና ልጨርስ። ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ ለተቃዋሚዎች የሰጧቸው መወዳደሪያና ማሸነፊያ አጀንዳ ህገ መንግስቱ እንዲሻሻል አደርጋለሁ የሚል እንደሆነ እገምታለሁ። ሰውየው አሁን ባለበት ሁኔታ ማሻሻል የሚዎስደውን ጊዜና ተግዳሮቶችን ጨምረው አብራርተዋል። ቢሆንም ማሻሻል የሚቻልበት እድል እንዳለም ሁኔታዎች ዝግ አለመሆናቸውን ጠቆም አድርገዋል። ነገር ግን አሁን ህገ መንግስቱ እንዲሻሻል አደርጋለሁ የሚል ፓርቲ አሸናፊነቱ ምንም ጥርጥር የለዉም ለማለት የፈለጉ ይመስላል፤ጆሮ ያለው ይስማ።

©አዲስ ተስፋ

ደሴምበር 2018